# የACPS Express 9/1/2022: የ‘Back to School’ ቅጾቻችሁን፣ ከ‘PowerSchool’ ቪዲዮ ጋር፣ አጠናቅቁ

## ቪዲዮ: የ‘Back to School’ ቅጾቻችሁን፣ በ‘PowerSchool’ አማካኝነት ያጠናቅቁ




ለእያንዳንዱ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - ልክ-እንደ አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት ብሎ እንደመቁጠር ቀላል-የሆነውን፤ የ‘Back to School’ ቅጾችን፣ በ‘PowerSchool’ ላይ ሙሉ። የማስተማሪያ ቪዲዮአችን፣ በእንግሊዘኛ/English እና ስፓኒሽ - እንዴት አስፈላጊ-የሆኑ ቅጾችን በ‘PowerSchool’ ላይ በመሙላት ጊዜያችሁ እንዳይጠፋ ለማድረግ እንደምትችሉ ያስረዳል:

- እንግሊዘኛ/English የ2022-23 የ‘Back to School’ ቅጾች
- ስፓኒሽ/Spanish የ2022-23 የ‘Back to School’ ቅጾች

የአማርኛ - እና አረብኛ-ቋንቋ ተናጋሪ ቤተሰቦች፤ ዳውንሎድ ተደርጎ የታተመውን የBack to School’ ጥራዝ/packetን - በኦንላይን ላይ በአማርኛ እና አረብኛ የሚገኘውን-በመሙላት፤ ወይም ጥራዙን (a packet) - ከልጃቸው ትምህርት ቤቶች በመጠየቅ እንዲያጠናቅቁም እናበረታታቸዋለን። እንግሊዘኛ- እና ስፓኒሽ-ቋንቋ ተናጋሪ ቤተሰቦች - የኤሌክትሮኒክ ዲቫይስ የሌላቸው ከሆኑም፤ ዳውንሎድ ተደርጎ የታተመውን የBack to School’ ጥራዝ/packetን - በኦንላይን ላይ በእንግሊዘኛ/English እና ስፓኒሽ የሚገኘውን-በመሙላት፤ ወይም ከትምህርት ቤታቸው የታተመውን ጥራዝ (a packet) በመጠየቅ፣ ማጠናቀቅ-ይችላሉ። ተሞልቶ-የተጠናቀቁ ቅጾች፤ ወደ ትምህርት ቤቱ የእንግዳ መቀበያ ቢሮ (front office) መግባት-አለባቸው።

እንደ የACPS ቤተሰብ አባልነት፤ ሁሉም-ተማሪዎች ለስኬት ዝግጁ-መሆናቸው በማረጋገጥ-ላይ ጠቃሚ-የሆነ ሚናን ትጫወታላችሁ። በአዲሱ የትምህርት ዓመት የመጀመሪያው ስራችሁ — በሴፕቴምበር (Sept.) 30 ቀን 2022 የሚያበቃውን፣ — እነዚህን የ‘Back to School’ ቅጾችን ሞልታችሁ ማጠናቀቅ ነው።

## ለነፃ የትምህርት ቤት ምግቦችን ለማግኘት - ማመልከቻን ማስገቢያ፣ የጊዜ-ገደቡ የሚያበቃበት ቀን እየተቃረበ ነው



ለቤተሰቦች፤ የ'ነፃ እና ቅናሽ-ዋጋ የተደረገላቸው ምግቦች (Free and Reduced-Price Meals (FARM)' ማመልከቻዎችን - ለ2022-23 የትምህርት ዓመት ሞልቶ-የማስገቢያው የጊዜ-ገደብ ማብቂያ-ቀን በፍጥነት-እየደረሰ ነው። የሣሙዔል ተከር (Samuel W. Tucker ) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ቤተሰቦች - ማመልከቻዎቻቸውን - እስከ **ሴፕቴምበር (Sept.) 8 ቀን 2022**፤ ማስገባት ያለባቸው፣ እና በሌሎቹ ሁሉም የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ-ቤተሰቦች፤ እስከ **ኦክቶበር (Oct.) 6 ቀን 2022**. ድረስ ማመልከቻዎቻቸውን ማስገባት አለባቸው።

ለተማሪ ምግቦች - የገንዘብ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ቤተሰቦች፤ ለ2021-22 የትምህርት ዓመት - ለነፃ እና ቅናሽ-ዋጋ የተደረገላቸው ምግቦች (Free and Reduced-Price Meals) ብቁ-ሆነው የነበሩ ወይም፣ በCommunity Eligibility Provision (CEP) ትምህርት ቤት ውስጥ ባለፈው ዓመት የተማሩ፤ የ'FARM' ማመልከቻ ቅጾችን አጠናቀቆ ለማስገባት - ተጨማሪ የ30-ቀን የሚኖራቸው ይሆናል።

የACPS ትምህርት ቤት የአመጋገብ አገልግሎቶች ቡድን (School Nutrition Services team)፤ ለሁሉም ቤተሰቦች፤ እስካሁን ካላደረጉት - የተማሪ የምግብ አካውንቶችን እንዲያስመዘግቡ (set up እንዲያደርጉ) ያበረታታል። ለቤተሰቦች፣ በኢሜል አማካኝነት ወይም በአሜሪካ ፖስታ/ቤት (U.S. Mail) አገልግሎት አማካኝነት፤ ከተማሪ የመታወቂያ (ID) ቁጥር እና የ'ፒን' (PIN) ቁጥር ጋር - የተማሪ አካነውንት ለትምህርት ቤት ምግቦች እንዴት በመመዝገብ  (set up በማድረግ) ማሰራት እንደምትችሉ የሚያሳየው-የመመሪያ ትዕዛዞች፣ ተልኮላችኋል። ቤተሰቦች ወደ አካውንቱ፤ ገንዘብ መጨመር፣ የተማሪውን የግዢ ሁኔታ መቆጣጠር፣ እና በኦንላይን ለማመልከት፤ ለFARM የማመልከቻ ሂደትን ለማካሄድ የሚያገለግለውን ማገናኛ (link)ን በመጠቀም ማመልከት ይችላሉ።

በ2022-23 የቀለም-ትምህርት ዓመት ወቅት የሚገኙ - ሁሉም የምግብ አገልግሎቶች፤ ከወረርሽኙ-በፊት ወደ-በነበረው የክንውን-ሂደት-አሰራራቸው ተመልሰዋል። ተማሪዎች፤ የACPS Community Eligibility Provision (CEP) ከሆኑት ስምንት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በአንደኛው-ውስጥ የማይማሩ፤ ወይም ለ'FARM' ብቁ-ያልሆኑ፤ ለቁርስ እና ምሣ ምግቦች ክፍያ-የሚከፍሉ ይሆናል፤ እና ቤተሰቦች ወደ ተማሪው አካውንቶች ውስጥ ገንዘብ መጨመር ያስፈልጋቸዋል። ማንኛውም ከዜሮ-በታች የሆነ የተማሪ የምግብ አጠቃላይ የገንዘብ-መጠን የነበረው ሁሉ፤ ሁሉን ተሰርዞ-የጠፋ እና ተመልሶ-ወደ $0.00 እንዲሆን ተደርጓል።

በ2022-23 የትምህርት ዓመት - የትምህርት ቤት ምግቦች የክፍያ-ዋጋ፣ እንደሚከተለው ናቸው:

- ከK-12 ክፍሎች-ውስጥ ለሆኑ - ቁርስ: $2.00 ነው።
- ከK-5 ክፍሎች-ውስጥ ለሆኑ - ምሣ: $3.05 ነው።

- ከ6-12 ክፍሎች-ውስጥ ለሆኑ - ምሣ: $3.25 ነው።
- የአዋቂ (Adult) ምግቦች: $4.00 ነው።

የ'Menu calendars'፤ ከK-5 ክፍሎች ውስጥ ለሚገኙ ለእያንዳንዱ ቤተሰቦች የሚሰጥ ይሆናል። በተጨማሪም 'menus' በትምህርት ቤት የአመጋገብ አገልግሎቶች፣ አፕ (app) አማካኝነት፣ እና [በACPS ድህረ-ገጽ] ላይ የሚገኙ ይሆናል።

## በየቀኑ በትምህርት ቤት: ACPS፣ አዎንታዊ-የሆነ በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት (Positive Attendance) በሴፕቴምበር (September) ወር ውስጥ - ያበረታታል



ሴፕቴምበር (September) ወር፤ በትምህርት-ገበታ ላይ የመገኘት ግንዛቤ-መስጫ ወር ነው፤ እና እያንዳንዱ ቀን ይቆጠራል! በየቀኑ ተማሪዎቻችን በሰዓቱ እና ለትምህርት-ዝግጁ ሆነው በትምህርት-ቤት ውስጥ መገኘታቸው፤ ለስኬታማ-ውጤታቸው ዕድልን-ፈጣሪ ነው። የዚህን ወር በዓል-አከባበር ለማስጀመር፣ እና በዚህ የትምህርት ዓመት ሙሉ አዎንታዊ-የሆነ በትምህርት-ገበታ መገኘትን ለማበረታታት፤ 'ሃሽታግ (hashtag) #SchoolEveryDay'ን እንጠቀማለን።

በትምህርት ቤት በመደበኛነት እና በሰዓቱ ተገኝቶ-መማር፤ በትምህርት ቤት ውስጥ እና የሕይወት ላይ - ከበርካታ አዎንታዊ-የሆነ ጥቅሞች-እንዳለው ታውቃላችሁ? ትምህርት ቤት በመደበኛነት እና በሰዓቱ ተገኝተው-የሚማሩ ተማሪዎች፤ ከሚከተሉት ጥቅም-ሊያገኙ ይችላሉ:

- ጠንካራ-የሆነ የቀለም-ትምህርት እና የማህበራዊ ችሎታዎችን ማሳደግ።
- አስተማሪዎች አቅደው-ያዘጋጁቸውን - ትምህርታዊ የፕሮግራም-አሰጣጥን ማግኘት።
- ከአስተማሪዎች እና ከእኩዮች ጋር፣ ጠንካራ ግንኙነቶችን መገንባት።
- የትምህርት ቤት እና የመማሪያ-ክፍል ማህበረሰብ አንዱ-አካል በመሆን መደሰት።
- በትምህርት ቤት ስራቸው እና በራሳቸው-የመማር ችሎታቸው ላይ የመኩራት-ስሜትን ማግኘት።
- ከእኩዮች ጋር፣ በትምህርታዊ-ተሞክሮዎች መካፈል።

መደበኛ-የሆነ በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት (attendance) መኖሩ፤ ለሚከተሉት ሊመራም-ይችላል:

- በክፍል-ደረጃ ላይ በመሆን ማንበብ፣ እና ከክፍል-ደረጃው በላይ ልቆ-መሄድን።
- የማስተዋል-ግንዛቤ ጥቅል-ማድረግ፣ አስተውሎ-ማሰብን፣ ምክንያቲያዊ የሆነ እና ችግሮችን የመፍታት ችሎታዎች።
- በሁሉም የትምህርት ዓይነት ዙሪያው-ባሉ ትምህርቶች በክፍል ውስጥ ማለፍ፤ እና ልቆ-መገኘት።
- ወደ ምርቃት የሚያደርሱ ክሬዲቶችን ማግኘት፣ እና ከምርቃት-በኋላ (postsecondary) ያሉ ዕቅዶችን መቅረጽ።
- ለኮሌጅ፣ ለስራ-መስክ እና ለሕይወት-ስኬት፤ አዎንታዊ-የሆነ በሰዓቱ-የመገኘት ልምድን-ማዳበር።

በመደበኛነት በትምህርት-ገበታ መገኘት (attendance) - በትምህርት ቤት ውስጥ ስኬታማ-ለመሆን እና - በትምህርት ቤት በየቀኑ እና በሰዓቱ ተገኝቶ መማርን ይገልፃል። በትምህርት-ገበታ ላይ መገኘት (attendance) በጣም-ጠቃሚ በመሆኑ-ምክንያት፤

ልጃችሁ ተላላፊ-የሆነ በሽታ ወይም ትኩሳት እስከሌለው ድረስ፤ እባካችሁ ወደ ትምህርት ቤት በየቀኑ ላኳቸው። በህመም-ምክንያት - ልጅዎ ከትምህርት ቤት መቅረት ካለበት፤ እባካችሁ የልጅዎን ትምህርት ቤት አሳውቁ።

በትምህርት-ገበታ መገኘት (attendance) ላይ የበለጠ-መረጃዎችን ለማግኘት፤ እባካችሁ - https://www.attendanceworks.org/ን ጎብኙ። አስታውሱ — ትምህርት ቤቶች፣ ቤተሰቦች እና የማህበረሰብ አጋሮች - እያንዳንዳቸው ተማሪዎች በ #SchoolEveryDay መማራቸውን ለማረጋገጥ ሁሉም-ሚና ይጫወታሉ። በዚህ ዓመት፣ ከእናንተ ጋር አብረን-ለመስራት በጉጉት እንጠባበቃለን!

## መልዕክቶችን-ከማግኘት ያለፈ-ነው: ከትምህርት ቤት ማህበረሰብ ጋር ለመሣተፍ፤ የ‘ParentSquare’ አፕ/Appን ዳውንሎድ-አድርጉ




በኦገስት (August) ወር ውስጥ፤ ACPS - አዲስ የግንኙነቶች መድረክ (communications platform)፣ ‘ParentSquare’፣ - ጠንካራ-የሆነ የትምህርት ቤትን-ከ-መኖሪያ-ቤት ጋር ማገናኘትን ለማበረታታት እና በሁሉም ትምህርት ቤቶቻችን ዙሪያ ወጥነት-ያለው አሰራር እንዲኖር ለማድረግ፤ በስራ-ላይ አውሎ አስጀምሯል። ሁሉም ቤተሰቦች - ከመዋዕለሕፃናት እስከ አስራ-ሁለተኛ ክፍል ያሉ ሁሉ፤ ይህን ቀላል እና አሳታፊ-የሆነ መድረክ/platformን ማግኘት ይችላሉ። የ‘ParentSquare’ ለተጠቃሚ-ቀላል የሆነ አቀማመጡ (user-friendly layout)፣ እና ሁሉን-አካታች የሆኑ የግንኙነት መሣሪያዎችን በአንድ-ላይ መያዙ፤ ቤተሰቦችን ለማግኘት የሚያስችለንን መንገድ እና፣ ቤተሰቦች እንዴት ከእኛ-ጋር ተሣታፊ መሆን እንደሚችሉ፣ በስፋት-የሚያቀርብ ነው።

የ‘ParentSquare’፣ መልዕክቶችን-ከመስጠት - ያለፈ ነው! ወዲያውኑ የትምህርት ቤት ማስታወቂያዎችን ከማግኘት በተጨማሪ፤ የቀሪ-ተማሪ ማስታወቂያዎች እና አስቸኳይ የሆኑ የማንቂያ-መልዕክቶችን - ቤተሰቦች ወደ ‘ParentSquare’ በሚመዘገቡ (sign up በሚያደርጉ-ጊዜ) ወይም አፑን (app) ዳውንሎድ ሲያደርጉ፤ የሚከተሉትን ማድረግ ይቻላል:

- ተመራጭ-የሆነውን የመገናኛ-ዘዴ(ዎች): ኢሜል፣ ቴክስት (text) እና/ወይም የሞባይል አፕ (mobile app) መምረጥ።
- ማስታወቂያዎችን፤ በየስንት-ጊዜ መቀበል እንደምትፈልጉ መወሰን — መልዕክቶች በዚያኑ-ቅጽበት የሚላክ (Instant)፣ ወይም በቀን-አንድ ጊዜ በ6 p.m. ላይ (Daily Digest) መወሰን።
- ሁለት-መንገድ ባለው የቀጥታ መልዕክቶችን መላኪያ-በመጠቀም ለአስተማሪዎች እና ለትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ በአውቶማቲክ በሚተረጉም (automated translation) በኩል መላክ።
- የክፍል፣ የትምህርት ቤት እና የክፍል-አቀፍ (division-wide) የሆኑ ዝግጅቶችን በአንድ-የቀን መቁጠሪያ ማጣመር።
- ለወላጅ-አስተማሪ ኮንፈረንሶች፣ መመዝገብ (Sign up ማድረግ)።
- የዲጂታል ፈቃድ-ማግኛ ወረቀቶች (digital permission slips)  ላይ መፈረም።
- የፎቶ-አልበሞችን፣ እና የዲጂታል በራሪ-ወረቀቶችን እና ፋይሎችን መመልከት።
- ከክፍል/division፣ ትምህርት ቤቶች፣ የመማሪያ-ክፍሎች እና የእንቅስቃሴ ቡድኖች፤ ግንኙነቶችን-በማድረግ - በአንድ-ማዕከላዊ በሆነ ቦታ ውስጥ ማስቀመጥ፣ እና ሌሎች ተጨማሪ ነገሮችንም ማድረግ።

ለACPS ግእር፣ በትምህርት ዓመቱ ሙሉ ግንኙነትን እያደረጋችሁ ለመቆየት ዝግጁ-መሆናችሁን እርግጠኛ ሁኑ! እባካችሁ፤ ‘ParentSquare’ን ከአፕል አፕ ስቶር/Apple App Store ወይም ጉግል ፕሌ ስቶር/Google Play Store ዛሬውኑ፣ ዳውንሎድ አድርጉ። በ‘PowerSchool’ ውስጥ በመዝገብ-ውስጥ ያለውን - የሞባይል ስልክ (cell phone) ቁጥርን ወይም የኢሜል አድራሻን በመጠቀም፤ አካውንታችሁ እንዲሰራ-አድርጉት (activate አድርጉት)።

መድረኩ (platform) ለሁሉም-ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረጋችንን እንቀጥላለን፤ ቤተሰቦች እና ሠራተኞች - መድረኩ (platform) ለመጠቀም የሚረዳቸውን በርካታ የመረጃ-ምንጮችን - በድህረ-ገፃችን ላይ በ www.acps.k12.va.us/parentsquare እናጋራለን።

## የሴፕቴምበር (Sept.) 8 ቀን 2022 - የትምህርት ቤት ቦርድ አጀንዳ



በሴፕቴምበር (Sept.) 8 ቀን 2022 ስብሰባው ላይ፣ የትምህርት ቤት ቦርዱ፤ የ2022-23 ‘Areas of Focus’ን እንደ ቀጣይነት ያለው ስራ የEquity for All 2025 Strategic Planን ለማሟላት - ይጠቀማል።

የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ አጀንዳዎችን እና ሰነዶችን ለማግኘት፤ Electronic School Boardን ይጎብኙ። ስብሰባዎችን በቀጥታ ለመመልከት እና ለመካፈል እንዴት እንደሚችሉ መረጃዎችን ለማግኘትም፤ በትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ድህረ-ገጽ መጎብኘት ትችላላችሁ።

## በኦገስት (Aug.) 25 ቀን 2022 - የአሌክሳንድርያ የCOVID-19 ማህበረሰብ ያለበት ደረጃ




እስከ ኦገስት (Aug.) 25 ቀን 2022 - ባለው-ጊዜ፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ የCOVID-19 ማህበረሰቡ-የሚገኝበት ደረጃ - ዝቅተኛ/low ሲሆን፤ ባለፉት ሰባት ቀናቶች ውስጥ፤  በየ100,000 ሰዎች፣ 198.8 ታማሚዎች አሉት። የበለጠ ለማወቅ፤ Alexandria COVID-19 dashboard ጎብኙ።

የመረጃ-ስብስቡ (data)፤ በመጨረሻ-እንዲስተካከል የተደረገው በኦገስት (Aug.) 25 ቀን 2022 ላይ እንደሆነ፣ እባካችሁ አስታውሱ። የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከል (Center for Disease Control and Prevention)፤ በሦስት ሜትሪክስ (three metrics) ጥምሮች ውስጥ - የCOVID-19 የማህበረሰብ የደረጃ-መጠንን ለመወሰን ተመልክቷል: አዲስ የCOVID-19 ታማሚ ሆነው የተመረመሩበትን በ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ፤ ገብተው-የተኙ በCOVID-19 ታካሚዎች የተያዙ አልጋዎች - በእያንዳንዱ የCOVID-19 በሽተኛ-ቁጥር፤ እና አጠቅላይ አዲስ የCOVID-19 ታማሚዎችን በየ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ ተመልክቷል።